ጤና ሚኒስቴር-ኢትዮጵያ
የዜጎች ጤና ለሀገር ብልፅግና!

**Ministry of Health - Ethiopia**
**Healthier Citizens for Prosperous Nation!**

ቀን / Date 3-12-2016

ቁጥር / Ref. No. መሚ1/49/39/1320

ለ፡ አፋር ብ/ክ/መ/ጤና ቢሮ
ለ፡ አማራ ብ/ክ/መ/ጤና ቢሮ
ለ፡ ኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጤና ቢሮ
ለ፡ ቤ/ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ጤና ቢሮ
ለ፡ ጋምቤላ ብ/ክ/መ/ጤና ቢሮ
ለ፡ ሶማሌ ብ/ክ/መ/ጤና ቢሮ
ለ፡ ሲዳማ ብ/ክ/መ/ጤና ቢሮ
ለ፡ ደቡብ ኢትዮጵያ ብ/ክ/መ/ጤና ቢሮ
ለ፡ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕ/ብ/ክ/መ/ጤና ቢሮ
ለ፡ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ብ/ክ/መ/ጤና ቢሮ
ለ፡ ሀረሪ ብ/ክ/መ/ጤና ቢሮ
ለ፡ አዲስ አበባ ከ/አስ/ጤና ቢሮ
ለ፡ ድሬዳዋ ከ/አስ/ጤና ቢሮ
ለ፡ ትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስ/ጤና ቢሮ
ለ፡ አ/አ/ከ/አስ/ም/መድሃኒት እና ጤና ተ/ቁ ባለስልጣን
ለ፡ ሶማሌ ብ/ክ/አስ/ምግብ፣ መድሃኒት እና ጤና ተ/ቁ ባለስልጣን
ለ፡ ጋምቤላ ብ/ክ/አስ/ም/መድሃኒት እና ጤና ተ/ቁ ባለስልጣን
ባሉበት

**ጉዳዩ፡- የ2017 የጤና ባለሙያዎች የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ (CPD) ትግበራ የአፈጥፃፀም መመርያን ይመለከታል፤**

በየደረጃው ባሉ ተቆጣጣሪ አካላት ለሚመዘገቡ የጤና ባለሙያዎች የሚሰጣቸዉ የሙያ ፈቃድ በሚታደስበት ጊዜ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ተግባራት አስፈላጊ በመሆኑ የአፈፃፀም መመርያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ የሚታወስ ነዉ፡፡ ስለሆነም የጤና ሚኒስቴር የጤናዉ ዘርፍ የሰዉ ሀብት ልማትና ማሻሻያ መሪ ስራ አስፈጻሚ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ስርዓትን በሁሉም ክልሎች ተግባራዊ እንዲደረግ በ2013 ዓ.ም የማስፈጸምያ መመርያ በማዉጣት ሰርኩላር ማስተላለፉ ይታወሳል፡፡

በዚህ አንድ ዓመት ዉስጥ ከተገኙት ልምዶች ፡ ካጋጠሙ ተግዳሮቶች እና ቀደም ብለው ስራ ላይ ከዋሉት የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ መመርያዎች በመነሳትና ሲሰራበት የነበረውን የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ማስፈፀምያ መመርያ (Manual) በማሻሻል ከሙያ ስራ ፈቃድ እድሳት ጋር ትስስሩን ለማስቀጠል ለቀጣይ አንድ ዓመት እንዲያገለገል ይህ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ማስፈፀምያ መመርያ ተዘጋጅቷል፡፡

በዚሁም መሠረት በ 2017 ዓ.ም በጀት ዓመት ከዚህ በፊት ተግባራዊ በሆነባቸው አስራ አንድ (11) የሙያ ዘርፎች ተግባራዊ እንዳታደርጉ እያሳሰብን ለአሰራሩ ያመች ዘንድ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ ከተያያዘዉ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ (CPD) ትግበራ የአፈፃፀም መመርያ 24 ገፅ የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

**ግልባጭ፡-**
- ለክቡር ሚኒስቴር ዴኤኤታ ጽ/ቤት (የጤናው ስራዎች አቅም ማጎልበቻ ዘርፍ)
- ለጤናና ጤና ነክ ተቋማት እና ባለሙያዎች ቁጥጥር መሪ ስራ አስፈጻሚ
- ለጤናዉ ዘርፍ የሰዉ ሃብት ልማትና ማሻሻያ መሪ ስራ አስፈፃሚ

**ጤና ሚኒስቴር**

+251-115-517011
+251-115-518031
+251-115-159657
+251-115-524549
+251-115-516378
+251-115-513301
Fax +251-115-519366
1234 Addis Ababa, Ethiopia
E-mail: moh@moh.gov.et
Website: www.moh.gov.et
Ministry of Health, Ethiopia
@FMoHealth

እባክዎን መልስ ሲሰጡ የእኛን ደብዳቤ ቁጥር ይጥቀሱ
**In Reply Please Refer to Our Ref.No.**

Scanned with CamScanner

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

የዜጎች ጤና ለሃገር ብልጽግና!
HEALTHIER CITIZENS FOR PROSPEROUS NATION!

# የ2017 ዓ.ም በጀት ዓመት የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ማስፈጸሚያ መመሪያ

# Continuing Professional Development (CPD) Implementation Manua for 2024/25

ነሐሴ 2016 ዓ/ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

MINISTRY OF HEALTH ETHIOPIA

Scanned with CamScanner

**ማውጫ**


ትርጓሜ....................................................................................................................iii

1. መግቢያ ................................................................................................................ 1

2. የመመሪያው አስፈላጊነት ............................................................................................ 1

3. ዝርዝር ዓላማዎች .........................................................................Error! Bookmark not defined.

4. የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴዎች ባህሪያት ..........................................Error! Bookmark not defined.

5. የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ጥቅም እና አስፈላጊነት ...........................................Error! Bookmark not defined.

6. የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴዎች የመረጃ አያያዝ ስርዓት ........................................................ 2

7. የተከታታይ ትምህርት መለኪያ (CEU) አሰጣጥ.................................................................................... 3

8. የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴዎች ተደራሽነት እና ፍትሃዊነት ...........Error! Bookmark not defined.

9. የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ አቅራቢዎች እና የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴዎች (ስልጠናዎች ጨምሮ)......... 5

10. የቅሬታ አያያዝ .................................................................................................. 5

11. ዋና ዋና የትግበራ አቅጣጫዎች ................................................................................ 5

12. ክትትል እና ግምገማ:- ........................................................................................ 8

13. የዕውቅና ሰጪዎች የምስክር ወረቀት........................................................................ 8

የማስፈጸሚያ እቅድ .........................................................................Error! Bookmark not defined.




Scanned with CamScanner

ትርጓሜ

1. **ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ :** ማለት ሚኒስቴሩ ባወጣው መመሪያ መሰረት ማንኛውም የጤና ባለሙያ በስራ ላይ እያለ በሙያው ያገኘውን እውቀትና ክህሎት ጠብቆ እንዲቆይ እና የሙያ ብቃቱን ለማጎልበት በየጊዜው የሚወስደው ሥልጠናና ሌሎች የሙያ ማጎልበቻ ስራዎች ናቸው ::
2. **የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴዎች፡** የጤና ባለሙያዎች ሊሳተፉባቸው እና ዕውቀታቸውንና ክህሎታቸውን ሊያሳድጉባቸው የሚችሉ ሲሆኑ በሁለት መደብ ይከፈላሉ። ይህም **ምድብ አንድ (Category I)** ማለት የስልጠና ማንዋል ተዘጋጅቶላቸው፤ ገጽ ለገጽ (face-to-face)፣ በበይነ መረብ (Online) ወይም ሁለቱን ባዋሃደ መልኩ የሚሰጥ ሲሆን **ምድብ ሁለት (Category II)** ማለት ደግሞ የጤና ባለሙያዎች በተለያየ መልኩ ሊሳተፉባቸው የሚችሉባቸው ሲሆኑ፤ (ዝርዝሩን በተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ መመሪያ ተካቷል)። ሁለቱም ዓይነት የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴዎች መስጠት የሚችሉት እውቅና በተሰጣቸው የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ አግለልጎት አቅራቢዎች (CPD providers) ብቻ ነው።
3. **የእውቅና ማረጋገጫ፡-** ለተለያዩ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ አቅራቢዎች (CPD providers) እና ለተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ኮርስ እና ተዛማጅ የሲፒዲ ተግባራት (CPD course and other CPD related activities) በገምጋሚዎች (CPD accredators) በኩል የሚሰጥ ማረጋገጫ ነው::
4. **እውቅና ሰጪ፡-** የተከታታይ ሙያ ማግልበቻ አገልግሎት አውቅና ሰጪ የምንላቸው የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ አገልግሎት ለሚያቀርቡ ተቋማትና ለሚዘጋጁ የስልጠና ማንዋሎች እውቅና የሚሰጡ የመንግስት ዩንቨርሲቲዎች እና የጤና ባለሙያዎች የሙያ ማህበራት ነው።
5. **የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻአገልግሎት ሰጭ(CPD providers)፡-** የመንግስት ወይም የግል ተቋማት ( ዩኒቨርስቲዎች፣ የጤና ሳይንስ ኮሌጆች፣የምርምር ተቋማት፣ የሙያ ማህበራት፣ ሆስፒታሎች እና ጤና ጣቢዎች) እና ሌሎች በጤናው ዘርፍ አማካሪ ድርጅቶች (Health consultancy firms) ሲሆኑ፣ ሚኒስትሩ ያወጣውን መመዘኛ ያሟሉ እና የማረጋገጫ እውቅና የተሰጣቸው ናቸው::

**አሰሪ፡-** የጤና ባለሙያዎች ሙያቸውን እንዲተገብሩ አጋዥ ባለሙያ የሚቀጥር አካል ነው::

MINISTRY OF HEALTH ETHIOPIA



አስግድ ሳሙኤል ቸሩ
የጤና ዘርፍ የሰው ሃብት ልማትና
ማኔጅመንት ዘርፍ ሥራ አስፈፃሚ

Scanned with CamScanner

1. መግቢያ

የጤና ባለሙያዎች ጥራት ያለው የጤና አጠባበቅ አገልግሎት ለመስጠት ያስችላቸው ዘንድ ሙያቸውን፣ እውቀታቸውን፣ ችሎታቸውንና አመለካከታቸውን በየጊዜው ማዳበርና ማሻሻል አለባቸው፡፡ ይህም በተለይ አዳዲስ በሽታዎች እየተከሰቱ መሆኑ፣ የበሽታዎች ባህሪይ እየተቀየረ በመምጣቱ፣ ጠፍተው የነበሩ በሽታዎች እንደገና ተመልሰው መታየት በመጀመራቸው፣ እና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እተበራከቱ በመምጣታቸው እንደ ዋነኛ ምክንያት ይወሰዳል፡፡

በርካታ ፈታኝ ጉዳዮች ባሉበት ከባቢያዊ ሁኔታ፣ ፈጣን ተቋማዊ ለውጦችና ፈጣን የቴክኖሎጅ ለውጦች እየታዩ ባሉበት ሁኔታ፣ እንዲሁም የደንበኞች ፍላጎት እየጨመረ በመምጣቱ የጤና ባለሙያዎች ሙያዊ ተወዳዳሪነትን ይዞ ለመቆየት ይችሉ ዘንድ በተከታታይ ሙያቸውን ማሻሻል ይኖርባቸዋል፡፡

ከዚህ አንጻር የጤና ሚኒስቴር በሀገሪቱ ያለውን የጤና አገልግሎት ጥራት እና ደረጃ ለማሻሻል በቁርጠኝነት እየሰራ ይገኛል፡፡ የኢትዮጵያ ጤና ፖሊሲ ባስቀመጠውና የጤናው ዘርፍ ሰው ሃብት ልማትና ማሻሻያ መሪ ስራ አስፈፃሚ ሊያተኩርባቸው ከሚገባቸው አምስት ስትራቴጂካዊ መስኮች አንዱ በጤናው ዘርፍ ለሁሉም የሙያ መስኮች ተገቢውንና ቀጣይነት ያለውን ትምህርትና ስልጠና ማዘጋጀት ነው፡፡ በተጨማሪም የጤና ሳይንስ ትምህርትና ሥልጠና ለአገሪቱ የጤና ፍላጎቶች ምላሽ የሚሰጥ መሆኑን ማረጋገጥ ከብሔራዊ የጤና የሰው ሃብት ስትራቴጂካዊ ዓላማዎች መካከል አንዱ ነው፡፡

ምንም እንኳን በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ አሰራር ደረጃውን ያልጠበቀ፣ ቁጥጥሩ ያልዳበረ እና ከፈቃድ እድሳት ጋር ያለው ትስስር ችግር ያለበት ቢሆንም የፌዴራል ጤና ሚኒስቴር ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በአሁኑ ወቅት ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ እና የስራ ላይ ስልጠናዎች አሰጣጥ ደረጃቸውን የጠበቁና ተቋማዊ እንዲሆኑ ለማስቻል እየሠራ ይገኛል፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ጤና ሚኒስቴር ደረጃውን የጠበቀ የጤና አገልግሎት ለማህበረሰቡ ለማድረስ ከሚያስችሉ ግብዓቶች አንዱ የሆነውን በስራ ላይ ያሉ የጤና ባለሙያዎችን እውቀት እና ክህሎት ለማጎልበት የሚያስችል የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ስርዓትን በመዘርጋት ለባለፈው አንድ ዓመት (3 ዓመት) ሲሰራ ቆይቷል። በዚህ ሶስት ዓመት ውስጥ ከተገኙት ልምዶች፣ ካጋጠሙን ተግዳሮቶች እና ቀደም ብለው ስራ ላይ ከዋሉ የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ መመሪያዎች በመነሳት እና ሲሰራበት የነበረውን የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ማስፈፀሚያ መመሪያ (Manual) በማሻሻል ከሙያ ስራ ፈቃድ እድሳት ጋር መተሳሰሩን ለማስቀጠል ለቀጣይ አንድ ዓመት እንዲያገለግል ይህ የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ማስፈፀሚያ መመሪያ (Manual) ተዘጋጅቷል።

2. የመመሪያው አስፈላጊነት

- የዚህ መመሪያ አስፈላጊነት በ2016ዓ.ም ሲሰራ የነበረው የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ማስፈፀሚያ መመሪያ (Manual) ካለው ነባራዊ ሁኔታ ሊያሰራ ባለመቻሉ፣ ከባለፈው ዓመት ካገኘነው ልምድ እና የአፈፃፀም ተግዳሮቶችን



MINISTRY OF HEALTH ETHIOPIA

Scanned with CamScanner

ለመፍታት እና የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ትግበራ ስርዓቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ጥራቱን በጠበቀ ደረጃ፤ የታለመለትን ዓላማ በሚያሳካ መንገድ ወጥነት ባለው መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ያለመ ነው። ይህ የማስፈፀሚያ ማንዋል በጊዚያዊነት በየዓመቱ የሚሸሻል ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ በዓመት ከአንድ ጊዜ በላይ ሊሸሻል ይችላል፡፡

3. የዚህ ሰነድ ዓላማ

- ለጤና ባለሙያዎች የተዘጋጀውን የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ መመሪያ አተገባበር ለማሳለጥ፤
- ዋና ዋናዎቹን የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴዎች ትግበራ አቅጣጫዎች ለመለየት፤
- ፣ የጤና ሚኒስቴር፣የክልል ጤና ቢሮ፣ የክልል ቁጥጥር አካላት፣ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ፍቃድ ሰጪዎች (CPD accreditors)ና አገለግሎት አቅራቢዎች (CPD providers) በመስተጋብር የሚሰሩበትን መንገድ ማሳየት
- ለተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴዎች ከትትልና ግምገማ ስርዓት አቅጣጫ ለማሳየት፤
- በተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ፐሮግራም ዉስጥ መሳተፋቸው ለሙያ ስራ ፈቃድ እድሳት በአስገዳጅ ሁኔታ የሚያስፈልጋቸው የሙያ ዘርፎችን መለየትና መወሰን
- ስለተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ሰነድ አደረጃጀት፣ ስለጥራት ማረጋገጫ አሰጣጥና ቁጥጥር እና ግምገማ አቅጣጫ ለመስጠት ነው፡፡

4. የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴዎች የመረጃ አያያዝ ስርዓት

4.1. በሚኒስቴሩ ውስጥ ያለው የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ዴስክ ቀጣይነት ያለው የሙያ ልማት የመረጃ ስርዓትን የማቆየትና የማዳበር ኃላፊነት አለበት፡፡ ኬዝ ቲሙ ለቀጣይ ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ትግበራ አስፈላጊ የሆኑ ቅጾችን በማዘጋጀት ድረ-ገፅ ላይ ያስቀምጣል፡፡

4.2. ከበይነ መረብ ላይ ሊገኙ የሚችሉ መመሪያዎችን፣ ቅጾችን፣ ተዛማጅ ሰነዶችን፣ ዕውቅና ያላቸው አቅራቢዎችን እና የኮርሶችን ዝርዝር በኤሌክትሮኒክ ቅጅዎች ወቅታዊ እያደረገ ድረ-ገፅ ላይ ያስቀምጣል፡፡

4.3. የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በተለያየ መልኩ ያሳተፏቸውን ባለሙያዎች ዝርዝር እና የተሳተፉባቸውን የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ተግባራት በዝርዝር በስልጠና ጊዜ ውስጥ በiHRIS ላይ ይሞላል ገና iHRIS ያልጀመሩ ካሉ ግን ስልጠናዉ ከተጠናቀቀ በ 5 ተከታታይ ቀናት ዉስጥ መላክ ይኖርባቸዋል።

4.4. አገር አቀፍ የመረጃ ቋት ተጠናቆ ስራ እስከሚጀምር በሁሉም አይነት ዘዴ (Online and face to face) የሚሰጡ የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ሰርተፊኬቶች (ማረጋገጫዎች) ባለሙያው የተዘጋጀውን የማጠቃለያ ሪፖርቱን (CPD activity summary report) ከተሰጡት ሰርቲፊኬቶች ጋር እዲያቀርብ ተደርጎ ተቆጣጣሪ አካላት ደግሞ የቀረበውን የማጠቃለያ ሪፖርቱን (CPD activity summary report) ትክክለኛነት በማረጋገጥ ማጠቃለያ ሪፖርቱን ብቻ ከባለሙያው ፋይል ጋር ማያያዝ አለበት፡፡



MINISTRY OF HEALTH ETHIOPIA

እስማኤል ባሙኤል ቶሩ
የሰው ሀብት ልማትና
ማኔጅመንት ስራ አስፈፃሚ

Scanned with CamScanner

የተከታታይ ትምህርት መለኪያ (CEU) አሰጣጥ

5.1. የተከታታይ ትምህርት መለኪያ (CEU) መስጠት የሚችሉት እውቅና የተሰጣቸው የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ አገልጎሎት አቅራቢዎች ብቻ ናቸው።

5.2. የተከታታይ ትምህርት መለኪያ (CEU) የሚሰጠውም የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡

5.3. የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ አገልጎሎት አቅራቢነት እውቅና የሌላቸው ተቋማት፣ የክልል ጤና ቢሮዎችን ወይም የክልል ተቆጣጣሪ አካላትን እና የፌዴራል ጤና ሚኒስቴርን ጨምሮ የተለያዩ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴዎችን ሲያዘጋጁ እውቅና ካላቸው ተቋማት ጋር የመግባቢያ ሰነዶችን በመፈራረም ለተሳታፊዎቻቸው የተከታታይ ትምህርት መለኪያ (CEU) ማስጠት ይችላሉ። በምስክር ወረቀቱ ላይም የጋራ ፈራሚ መሆን ይችላሉ።

5.3.1. የተሳታፊዎች መረጃ በተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ አገልግሎት አቅራቢዎች በኩል መሰብሰብና መቀመጥ አለበት፡፡

5.3.2. የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴዎች ጥራት በሁለቱም በኩል መጠበቅ ቢኖርበትም የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ አገልግሎት አቅራቢዎች ኃላፊነት ይሆናል፡፡

5.3.3. የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ አገልግሎት አቅራቢዎች የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴዎች ሲያካሄዱ መገኘት አለባቸው፡፡

5.4. የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴዎች የተከታታይ ትምህርት መለኪያ (CEU) እንዲሰጣቸው መከናወን ያለባቸው በበጀት ዓመቱ ብቻ ነው። ይህ ሁለቱንም የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴ መደቦች ይመለከታል፡፡

5.5. አንድ የጤና ባለሙያ አንድ ርዕስ ባለው የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴ ከአንድ ጊዜ በላይ የተከታታይ ትምህርት መለኪያ (CEU) ሊሰጠው አይገባም። ነገር ግን ርዕሱና አላማው የተለያየ ከሆነ ያለገደብ ሊሰጠው ይችላል።

5.6. የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻን ከሙያ ስራ ፈቃድ እድሳት ጋር ማስተሳሰር።

አሰግድ ሳሙኤል ቸሩ

MINISTRY OF HEALTH ETHIOPIA



Scanned with CamScanner

5.7. በ2017 በጀት ዓመት የሙያ ፈቃድ ለሚያሳድሱ ባለሙዎች ሌሎች መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉትን መስፈርቶች ሲያሟሉ የሙያ ስራ ፈቃዳቸው ይታደስላቸዋል፡-

5.7.1. በ2015 እና 2016 በጀት ዓመት ከሚጠበቅባቸው በጥቅሉ 60 CEU እና ከዚያ በላይ ከሀምሌ1/2016 ዓም እስከ መስከረም 30/2017 ዓ.ም ለሚያሳድሱ 7.5 CEU በድምሩ ከ 67.5 CEU ሲያቀርቡ የሙያ ስራ ፍውቃዳቸው ይታደስላቸዋል።

5.7.2. ከጥቅምት 1/2017 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30/2017 ለሚመጡ ደግሞ 15 CEU በድምሩ 75 CEU ሲያቀርቡ የሙያ ስራ ፍውቃዳቸው ይታደስላቸዋል።

5.7.3. ከጥር 1/2017 ዓ.ም እስከ መጋቢት 30/2017 ለሚመጡ ደግሞ 22.5 CEU በድምሩ 82.5 CEU ሲያቀርቡ የሙያ ስራ ፍውቃዳቸው ይታደስላቸዋል፡፡

5.7.4. ከሚያዚያ 1/2017 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2017 ለሚመጡ ደግሞ 30 CEU በድምሩ **90** CEU ሲያቀርቡ የሙያ ስራ ፍውቃዳቸው ይታደስላቸዋል፡፡

**5.7. በ2016 ዓም በጀት አመት ትስስር የጀመሩ ክልሎች የዓመቱን በጥቅሉ 30 CEU የሚያመጡ ይሆናል።**

5.7.1. በ 2017 ከሀምሌ 1/2016 እስከ መስከረም 30/2017 ዓ.ም ለሚያሳደሱ 37.5 CEU ሲያቀርቡ የሙያ ስራ ፍውቃዳቸው ይታደስላቸዋል።

5.7.2. በ 2017 ዓም ከጥቅምት1/2017 ዓም እስከ ታህሳስ 30/2017 ዓ.ም ለሚያሳደሱ 45 CEU ሲያቀርቡ የሙያ ስራ ፍውቃዳቸው ይታደስላቸዋል።

5.7.3. በ 2017ዓም ከጥር 1/2017 ዓም እስከ መጋቢት 30/2017 ዓ.ም ለሚያሳደሱ 52.5 CEU ሲያቀርቡ የሙያ ስራ ፍውቃዳቸው ይታደስላቸዋል።

5.7.4. በ 2017 ሚያዝያ 1/2017 ዓም እስከ ሰኔ 30/2017 ዓ.ም ለሚያሳደሱ **60** CEU ሲያቀርቡ የሙያ ስራ ፍውቃዳቸው ይታደስላቸዋል።

5.8. ትስስር ካልጀመሩ ክልሎች ወደ ጀመሩ ክልሎች የተዘዋወሩ የጤና ባለሙያዎች አሁን ወደተዘዋወሩበት ክልል እንደየቆይታቸው ጊዜ ታሳቢ ተደርጎ (በወር 2.5) ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

**5.9. በ2017 ትስስር የሚጀመሩ ክልሎች በዓመቱ መጨረሻ ላይ 30 CEU ለሙያ ፈቃድ እድሳት ያስፈልጋል፡፡**

5.9.1በ 2017 ሀምሌ 1/2016ዓም እስከ መስከረም 30/2017 ዓ.ም ለሚያሳደሱ 7.5 CEU ሲያቀርቡ የሙያ ስራ ፍውቃዳቸው ይታደስላቸዋል።

5.9.2በ 2017 ጥቅምት1/2017 ዓም እስከ ታህሳስ 30/2017 ዓ.ም ለሚያሳደሱ 15 CEU ሲያቀርቡ የሙያ ስራ ፍውቃዳቸው ይታደስላቸዋል።

5.9.3በ 2017 ጥር1/2017 ዓም እስከ መጋቢት 30/2017 ዓ.ም ለሚያሳደሱ 22.5 CEU ሲያቀርቡ የሙያ ስራ ፍውቃዳቸው ይታደስላቸዋል።

5.9.4በ 2017 ሚያዝያ 1/2017 ዓም እስከ ሰኔ 30/2017 ዓ.ም ለሚያሳደሱ 30 CEU ሲያቀርቡ የሙያ ስራ ፍውቃዳቸው ይታደስላቸዋል።



MINISTRY OF HEALTH ETHIO...

አስግድ ሳሙኤል (ዶ/ር)
የጤና ዘርፍ የሰው ሃብት ልማት
ማሻሻያ መሪ ሥራ አስፈፃሚ

Scanned with CamScanner

5. የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ አቅራቢዎች እና የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴዎች (ስልጠናዎችን ጨምሮ)

6.1. ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ እና ከዚያ በኋላ ሁሉም ስልጠናዎች ዕውቅና ባለው የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ማእከል እና ኮርስ መሰጠት አለባቸው፡፡

6.2. ዕውቅና ካለው የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ማዕከል እና ኮርስ የተሰጠ የምስክር ወረቀት ለሙያ ፈቃድ እድሳት ያገለግላል፡፡

6.3. የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ አገልግሎት አቅራቢዎች ከሥልጠና በተጨማሪ በምድብ ሁለት የተዘረዘሩትን እንቅስቃሴዎች ሚንስትር መስሪያ ቤቱ በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት በተቀናጀና ስርዓት ባለው መልኩ ማቅረብ ይችላሉ፤

**ማስታወሻ:-**

1. በጤና ሚ/ር የተዘጋጀውን የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ (directive and guidline) ይመልከቱ፡፡
2. ለአፈፃፀም ይረዳ ዘንድ ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዘውን ዕዝል 2 እና 3 ይመልከቱ፡፡

6. ቅሬታ አያያዝ

ማንኛውም ባለሙያ፣የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ማዕከል ወይም ፈቃድ ሰጪ አካል ያለው ቅሬታ በተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ መመሪያ(Directive) መሰረት በማድረግ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ላይ ባለው ይስተናገዳሉ፡፡

**ዋና ዋና የትግበራ አቅጣጫዎች**

6.1. የጤና ሙያ የምድብ ዓይነቶችንና ሊሳተፉባቸው ስለሚገባ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴዎች መለየት:-

8.1.1 የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ስልታዊ በሆነ መንገድ ከተመረጡ የጤና ሙያዎች ፈቃድ እድሳት ጋር ይገናኛል፡፡ በሂደት ሁሉም የጤና ሙያዎች ይካተታሉ፡፡ እነዚህን ለማከናወን የጤናና ጤና ነክ ተቋማትና ባለሙያዎች ቁጥጥር መሪ ስራ አስፈፃሚ፣ የጤናው ዘርፍ የሰው ሀብት ልማትና ማሻሻያ መሪ ስራ አስፈፃሚ፣ የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ዴስክ የብሔራዊ ተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮሚቴ እና የክልል ጤና ቢሮ/ተቆጣጣሪ አካላት ይህን ተግባር ለማከናወን ሃላፊነት ይወስዳሉ፡፡

8.1.2 የጤና ባለሙያዎች ሊሳተፉባቸው የሚገባ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴ ዘርፎች ለመለየት የጤና ባለሙያዎች ማህበራት፣ የብሔራዊ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮሚቴ እና በጤና ሚኒስቴር የሰው ሀብት ልማት ዳይሬክቶሬት ኃላፊነት ይኖርባቸዋል። የተለዩትም ዘርፎች ለጤና ባለሙያዎች በሚገባ መገለጽ ይኖርባቸዋል። ለዚህም የጤና ተቋማትን መሰረት ያደረጉ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ አገልግሎት አቅራቢዎችና የሙያ ማህበራት ጉልህ ሚና መጫወት አለባቸው።

8.1.3 የእውቅና ሰጪ አካላትና የክልል ጤና ቢሮ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ቡድን/የክልል ተቆጣጣሪ አካላትን በጋራ በመሆን የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪ ተቋማትን ምዘናና እውቅና አሰጣጥ ስርዓትን በጋራ ያካሂዳሉ፡ ፡

MINISTRY OF HEALTH ETHIOPIA

አለማየሁ ሳሙኤል ቾሬ
የጤና ዘርፍ የሰው ሃብት ልማትና
ማሻሻያ መሪ ሥራ አስፈፃሚ



Scanned with CamScanner

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴዎች እና የፈቃድ እድሳት የሚጠየቁ የጤና ሙያዎች ናቸው፡

-

| | |
|---|---|
| ▪ በነርሲንግ | ▪ BSC nurse<br>▪ Surgical nurse<br>▪ Pediatric nurse<br>▪ OR Nurse<br>▪ Emergency and critical care nurse<br>▪ Emergency and intensive care nurse<br>▪ Neonatal Nursing<br>▪ Psychiatry nurse |
| ▪ የጤና መኮንን | HO |
| ▪ ሚድዋይፍሪ | BSC |
| ▪ ፋርማሲ | BSC in pharmacy/ Pharmacy<br>ClinicalPhramcy |
| ▪ የህክምና ላቦራቶሪ ቴክኖሎጂ | BSC in medical Laboratory technonology |
| ▪ አንስቴዥያ | Bsc in Anesthesia |
| ▪ ህክምና ሳይንስ ስፔሻሊስቶችን ጨምሮ | GP<br>Specialist<br>Subspecialist<br>Superspecialist |
| ▪ የጥርስ ህክምና | BSC in Dental Health<br>MD in Dentistry<br>Specialist<br>Subspecialist<br>Superspecialist |



MINISTRY OF HEALTH ETHIOPIA

አስግድ ሳሙኤል ቸሩ
ጤና ዘርፍ የሰው ሃብት ልማት
ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

Scanned with CamScanner

| | |
|---|---|
| ▪ Environmental health professtionals | BSC in Enviromental health |
| ▪ Biomedical engineering | BSC in Biomedical Engineering |
| ▪ Physiotherapy | BSC in physiotherapy |

**6.2. የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ስርዓትን ከሰው ሃብት መረጃ ስርዓት ጋር ማስተሳሰር፡-**

8.2.1 ጤና ሚኒስቴር/የጤናው ዘርፍ የሰው ሀብት ልማትና ማሻሻያ መሪ ስራ አስፈፃሚ/ የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ዴስክ የiHRIS አተገባበሩን በዋናነት የመረጃ አያያዝ ስርዓቱን ያበለፅጋል፣ ስልጠና ይሰጣል፣ድጋፍና ክትትል ያደርጋል::

8.2.2. የክልል ጤና ቢሮዎች እና የክልል የተቆጣጣሪ አካላት የሰው ሀብት መረጃ አያያዝ ስርዓት የመጠቀም፣ የማጠናከርና የመከታተል ኃላፊነት አለባቸው::

8.2.3. በጤና ሚኒስቴር ውስጥ ያለው የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ዴስክና የብሔራዊ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮሚቴ በፈቃድ ሰጪውና በአቅራቢው ደረጃ ያለውን የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ መረጃ አያያዝ ይከታተላሉ::

8.2.3. ሁሉም የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ እውቅና ሰጭዎችና አቅራቢዎች በተሰጣቸው ስልጣን ዕርከን መሰረት iHRISን ሙሉ በሙሉ ይተገብራሉየተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ እውቅና ሰጭዎችና አቅራቢዎች የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ተግባራትን iHRISን በመጠቀም ሪፖርት ያደርጋሉ!

**6.3. የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴዎችን መለየት እና ማከናወን፡-**

8.3.1. የተከታታይ የሙያ ሙያ ማጎልበቻ አገልግሎት አቅራቢዎች የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ተግባራት ማከናወን የሥልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድንና ሥልጠናውን በአካልና በበይነ መረብ አማካኝነት (Online) መስጠት፣ በመደብ ሁለት (Category II) የተቀመጡ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴዎችን በተቀመጠው መመሪያ መሰረት መለየትና መስጠት፣ መስፈርቱን አሟልተው ለጨረሱ የጤና ባለሙያዎች የተከታታይ ትምህርት መለኪያ (CEU) የምስክር ወረቀት መስጠትን፣ ጥራቱን የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ እንዲሁም ለሚመለከታቸው አካላት ጊዜውን የጠበቀ ሪፖርት መላክን ያካትታል። ከዚህ በተጨማሪ የጤና ባለሙያው ስለተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴዎች በቂ መረጃ እንዲያገኙ ማድረግም ይጠበቅባቸዋል።



MINISTRY OF HEALTH ETHIOPIA

Scanned with CamScanner

8.3.2. የሙያ ማጎልበቻ አገልግሎት እውቅና ሰጭዎች፣ የክልል ጤና ቢሮ ፣ የሙያ ማህበራት፣የጤና ሚኒስቴርና የብሔራዊ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮሚቴ እንቅስቃሴዎችን/ተግባራትን የመከታተል ሃላፊነቱን ይወስዳሉ፡፡

8.4. **የምስክር ወረቀት አሰጣጥ፡-** ሁሉም የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ አገልግሎት አቅራቢዎች ለተሳታፊዎች የብቃት/የማጠናቀቂያ/ የተሳትፎ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት አለባቸው፡፡ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴዎች ቆይታ በተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ መመሪያ መሠረት ወደ ተከታታይ ትምህርት መለኪያ (CEU) መለወጥ አለባቸው፡፡

8.5. **የኮርስ ኮድ አቅርቦት፡-** የጤና ሚኒስቴር የኮርስ መደራረብን ለማስቀረት ልዩ ኮድ ለእውቅና ሰጭዎች ይሰጣል፡፡ የጤና ሚኒስቴር በተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ መመሪያ እና አቅጣጫ መሰረት ለኮርሶች ልዩ ኮድ የማቅረብ ሃላፊነት አለበት፡ ፡

7. **ክትትል እና ግምገማ፡-**

9.1. የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ቁጥጥር እና ግምገማ በጤና ሚኒስቴር እና በክልል ጤና ቢሮዎች/ በክልል ተቆጣጣሪ አካላት፣ የብሔራዊ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮሚቴ እና በተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ እውቅና ሰጭዎች በመደበኛነት ይከናወናል፡፡

9.2. **ክትትል ሊደረግባቸው የሚገቡ ተግባራት፡-**

- **የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሂደት፡-**
    - ➢ ተከታታይ የሙያ ስልጠና ኮርሶች ዕውቅና አሰጣጥ ሂደቶች፣
    - ➢ (የዘርፉን ባለሙያዎች፣ የስርዓተ-ትምህርት፣ የትምህርት አሰጣጥ ንድፍ እና የፕሮግራም ባለሙያዎችን ማሳተፉን)፡
    - ➢ የተከታታይ ትምህርት መለኪያን መሠረት በማድረግ ለተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ አገልግሎት ሰጪዎች እውቅና የመስጠት፣ ለጤና ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ የማደስ ሂደቶች፣
- አቅራቢዎች የሚፈለጉትን ደረጃዎች ማሟላታቸው
- ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ አገልግሎት ፍላጎቶች እና በተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ውስጥ የጤና ባለሙያዎች ተሳትፎ ደረጃ፣ አሰልጣኞች፣ ርዕሶች፣ የማስተማሪያ ዘዴዎች፣ የሥልጠና መሳሪያዎች ጥራትና አቅርቦት እንዲሁም የመማርያ ከባቢያዊ ተገቢነት ክትትል ሊደረግባቸውና ሊገመገሙ ይገባል፡፡
- በጥንቃቄ የታቀደና ስርዓት ባለው መንገድ ከተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ተሳታፊዎች ግብረመልስ መሰብሰብ፣ መተንተን እና በተገኘው ውጤት መሰረት ማስተካከያ በማድረግ ይህንንም ለባለድርሻ አካላት ማቅረብ ፡፡
- በተጨማሪም የመማር ሂደቱን (አደረጃጀቱን እና ሀብቱን እንዲሁም የመማሪያ አካባቢን ጨምሮ) ፣ ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ አወቃቀርን (የፕሮግራም መግለጫ እና የታሰበውን ውጤት ያካተቱ) እና የመማር ውጤቶችን ማየት

8. **የዕውቅና ሰጪዎች የምስክር ወረቀት**



MINISTRY OF HEALTH ETHIOPIA

አስማድ ሳሙኤል ቸሩ
የጤና ዘርፍ የሰው ሃብት ልማትና
ማሻሻያ መሪ ሥራ አስፈፃሚ

Scanned with CamScanner

የዕውቅና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በሚኒስቴሩ የሚሰጥ ሲሆን አመልካቾች ፈቃዱ ከማብቃቱ/ከማለቁ ከሁለት ወር በፊት ለእድሳት ማመልከት ይኖርባቸዋል::

- የምስክር ወረቀቱ ደረጃውን የጠበቀ መሆን አለበት::
- የምስክር ወረቀቱ የመለያ ኮድ ሊኖረው ይገባል::
- የዕውቅና ሰጪዎች የምስክር ወረቀታቸውን በሚታይ ቦታ ማስቀመጥ አለባቸው::

9. አስተዳደራዊ እርምጃዎች

- 14.1. የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ስልጠና ለሚሰጡ ተቋማት እውቅና የሚሰጡ ተቋማት /Accreditors/ እና የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ሰጪ ተቋማት /CPD providers/ ከተሰጣቸው የአሰራር መመሪያ፣ ደንብ ውጭ ሲሰሩ ከተገኙ በመመሪያው (Directive) መሰረት በጤና ሚኒስቴር በኩል ጥብቅ እርምጃ ይወስዳል::

የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ አክሪዲተሮች የስልጠና አቅራቢዎችን አፈጻጸም በመገምገም የማስተካከያ እርምጃዎች ይወስዳሉ

MINISTRY OF HEALTH ETHIOPIA



Scanned with CamScanner

## አዝል 1 በጤና ባለሙያ ለሙያ ማደሻ የሚቀርብ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ መለኪያ(CEU) ማጠቃለያ ቅፅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

[የክልል ስም ይግባ]

[የተቆጣጣሪ አካል ስም ይግባ]

የአመልካች ሙሉ ስም ________________________

የሙያ ዘርፍ ________________________ የአመለከቱበት ቀን________________________

| ተቁ | የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ርዕስ | የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ዓይነት (CPD modality, eg: training, workshop, grand round, etc) | የተገኘው የተከታታይ ትምህርት መለኪያ (CEU ) | የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ እንቅስቃሴው የተካሄደበት ማዕከል | የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻው የተካሄደበት ቀን | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

ያረጋገጠው ባለሙያ ስም:------------------------------------------ ፊርማ: -------------------------- ቀን:----------------



Scanned with CamScanner

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA
የዜጎች ጤና ለሃገር ብልፅግና!
HEALTHIER CITIZENS FOR PROSPEROUS NATION!

**National Continuing Professional Development Committee (NCPDC)**

## Category II CPD Activities CEU Allocation Checklist

| SN | Criteria | Status |
|---|---|---|
| 1 | Name of the applicant (Individual or department) | ______________________ |
| 2 | Title of the Category II CPD Activity is well written? | ☐ Yes<br>☐ No |
| 3 | Venue (Place) is known | ☐ Yes<br>☐ No |
| 4 | Date (dd/mm/yy) is written | ☐ Yes<br>☐ No |
| 5 | Duration of the grand round (hh:mm: ss) is written | ☐ Yes<br>☐ No |
| 6 | Presenter (s) full name (First, Middle, and Last) is well written | ☐ Yes<br>☐ No |
| 7 | Author (s) name (First, Middle, and Last) for a book, research, a case report is well written? | ☐ Yes<br>☐ No |
| 8 | Objective (s) of the Category II CPD Activity is identified and listed | ☐ Yes<br>☐ No |
| 9 | Brief Summary of the Category II CPD Activity (Optional) is documented | ☐ Yes<br>☐ No |
| 10 | List of Names of Participants (First, Middle, and Last) with their signature is documented | ☐ Yes<br>☐ No |
| 11 | Is the application form authorized by the applicant (full name, signature, and titer for deaprtments) | ☐ Yes<br>☐ No |

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH ETHIOPIA

አስግድ ሳሙኤል (ዶ/ር)
የጤና ዘርፍ የሰው ሃብት ልማትና
ማሻሻያ መሪ ሥራ አስፈፃሚ



Scanned with CamScanner

[Please enter the hospital's or Facility's Logo here]

[Please enter the name of the hospital/facility here]

Grand Round Sessions/Case Management Reporting format

[Enter Department Name Here]

| | |
|---|---|
| **Title of the Grand Round /Case Management** | |
| **Venue (Place)** | |
| **Date (dd/mm/yy)** | |
| **Duration of the grand round (hh:mm: ss)** | |
| **Presenter (s) Name (First, Middle, and Last)** | |
| **Moderator (s) Name (First, Middle, and Last)** | |
| **Brief Case Summary of the grand round /Case Management** | |
| **Objective (s) of the grand round /Case Management** | |

MINISTRY OF HEALTH ETHIOPIA

Scanned with CamScanner

[Please enter the hospital's or Facility's Logo here]

[Please enter the name of the hospital/facility here]

## Grand Round Sessions/Case Management Reporting format

[Enter Department Name Here]

List of Participants

| No | Title | Full Name (First, Middle, Last) in BLOCK LETTERS | Profession | Department (s) Represented | Remark |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Dr | | | | |
| 2 | Prof | | | | |
| 3 | Nr | | | | |
| 4 | | | | | |
| 5 | | | | | |
| 6 | | | | | |
| 7 | | | | | |
| 8 | | | | | |

**NB: 1. The department must submit this form after every grand round /Case Management Session to the office of CPDC.**

**2. The department head must sign and put her /his titer on every page of this reporting format**



Scanned with CamScanner

[Please enter the hospital's or Facility's Logo here]

[Please enter the name of the hospital/facility here]

Morning Sessions Reporting format

[Enter Department Name Here]

| | |
|---|---|
| **Venue (Place)** | |
| **Date (dd/mm/yy)** | |
| **Duration of the morning session (hh:mm: ss)** | |
| **Presenter (s) Name (First, Middle, and Last)** | |
| **Moderator (s) Name (First, Middle, and Last)** | |
| **Brief Case Summary (s) of the morning session** | |
| **Objective (s) of the morning session** | |



Scanned with CamScanner

[Please enter the hospital's or Facility's Logo here]

[Please enter the name of the hospital/facility here]

Morning Sessions Reporting format

[Enter Department Name Here]

List of Participants

| No | Title | Full Name (First, Middle, Last) in BLOCK LETTERS | Profession | Service Unit (s) | Remark |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Dr | | | | |
| 2 | Prof | | | | |
| 3 | Nr | | | | |
| 4 | | | | | |
| 5 | | | | | |
| 6 | | | | | |
| 7 | | | | | |
| 8 | | | | | |

**NB: 1. The department must submit this form after every week on Friday.**

**2. The department head must sign and put her /his titer on every page of this reporting format**

MINISTRY OF HEALTH ETHIOPIA



Scanned with CamScanner

[Please enter the hospital's or Facility's or Professional Association Logo here]

[Please enter the name of the hospital/facility/Professional Association here]

Seminar/Panel Discussion Reporting format

[Enter Department Name Here]

| | |
|---|---|
| **Title of the Seminar/Panel Discussion** | |
| **Venue (Place)** | |
| **Date (dd/mm/yy)** | |
| **Duration of the grand round (hh:mm: ss)** | |
| **Presenter/Panelist (s) Name (First, Middle, and Last)** | |
| **Moderator (s) Name (First, Middle, and Last)** | |
| **Summary of the Seminar /Panel Discussion** | |
| **Objective (s) of the seminar/Panel Discussion** | |

MINISTRY OF HEALTH ETHIOPIA



Scanned with CamScanner

[Please enter the hospital's or Facility's or Professional Association Logo here]

[Please enter the name of the hospital/facility/Professional Association here]

Seminar/Panel Discussion Reporting format

[Enter Department Name Here]

List of Participants

| No | Title | Full Name (First, Middle, Last) in BLOCK LETTERS | Profession | Department (s) Represented | Remark |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Dr | | | | |
| 2 | Prof | | | | |
| 3 | Nr | | | | |
| 4 | | | | | |
| 5 | | | | | |
| 6 | | | | | |
| 7 | | | | | |
| 8 | | | | | |

**NB: 1. The department must submit this form after every seminar to the office of CPID.**

**2. The department head must sign and put her /his titer on every page of this reporting format**



Scanned with CamScanner

[Please enter the hospital's or Facility's or Professional Association Logo here]

[Please enter the name of the hospital/facility/Professional Association here]

Workshop Reporting format

[Enter Department Name Here]

| | |
|---|---|
| **Title of the workshop** | |
| **Venue (Place)** | |
| **Date (dd/mm/yy)** | |
| **Duration of the workshop (hh:mm:ss)** | |
| **Brief Summary of the workshop** | |
| **Objective (s) of the workshop** | |

MINISTRY OF HEALTH ETHIOPIA



Scanned with CamScanner

[Please enter the hospital's or Facility's or Professional Association Logo here]

[Please enter the name of the hospital/facility/Professional Association here]

Workshops Reporting format

[Enter Department Name Here]

List of Participants

| No | Title | Full Name (First, Middle, Last) in BLOCK LETTERS | Profession | Department (s) Represented | Remark |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Dr | | | | |
| 2 | Prof | | | | |
| 3 | Nr | | | | |
| 4 | | | | | |
| 5 | | | | | |
| 6 | | | | | |
| 7 | | | | | |
| 8 | | | | | |

**NB: 1. The department must submit this form after every workshop to the office of CPID.**

**2. The department head must sign and put her /his titer on every page of this reporting format**



Scanned with CamScanner

[Please enter the hospital's or Facility's or Professional Association Logo here]

[Please enter the name of the hospital/facility/Professional Association here]

Research/Case Report Reporting format

[Enter Department Name Here]

| | |
|---|---|
| **Title of the research/case report** | |
| **Date Published** | |
| **Journal (the research/case report published on)** | [Write its name, volume, issue, and website here] |
| **Type of research** | |
| **PI's Name (First, Middle, and Last)** | |
| **Collaborator (s) Name (First, Middle, and Last)** | |
| **Brief Case Summary or Abstract of the research or case report** | [Please attach the link or copy of the abstract with this report] |
| **Objective (s) of the research or case report** | |

**The applicant's name**____________________________

**Date of application for CEU**________________________

**Signature**__________________________________



Scanned with CamScanner